www.abyssinialaw.com




| | |
|---|---|
| 17ኛ አመት ቁጥር 19<br>17th Year No 19 | ባህር ዳር ነሀሴ 1 ቀን 2004 ዓ.ም<br>Bahir Dar 7th August, 2012 |


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 14.615 Price Birr | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የ ፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |


| ማውጫ | Contents |
|---|---|
| **ደንብ ቁጥር 100/2004 ዓ.ም** | **Regulation No.100/2012** |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ልማት አጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Information and Communication Technology Development Agency Establishment Regulation Amendment, Council of Regional Government Regulation |

| ደንብ ቁጥር 100/2004 ዓ.ም | REGULATION NO. 100/2012 |
|---|---|
| በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ልማት አጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO AMEND THE INFORMATION AND COMMUNICATION TECHNOLOGY AGENCY ESTABLISHMENT REGULATION IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE |

www.abyssinialaw.com



በክልሉ ያለውን የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ እንቅስቃሴ ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በአነስተኛና በመካከለኛ ደረጃ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ቢዝነስ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩትን ሥራ ፈጣሪዎች ዕድገት ለማፋጠንና በአጀማመራቸው ወቅት የሚያጋጥማቸውን መሰናክል በመቀነስ ለክልሉና ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማበርከት የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

WHEREAS, it has been necessary to create a favourable condition enabling those small and medium level entrepreneurs to be engaged in the business activities of the Information and Communication Technology so that they would contribute their share to the economic development of the region and the country as a whole by minimizing the constraints which they may face as of the time of the start up and to accelerate their development so as to make more effective the existing operation of the Information and Communication Technology in the Region;

በአሁኑ ወቅት የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ዘርፍ ካለበት የባለሙያ እጥረትና ኅብረተሰቡ በዘርፉ ያለውን ተጠቃሚነት ከማጎልበት አንጻር ሥራ ፈጣሪዎች ያላቸውን ጊዜና ገንዘብ በማቀናጀት አስፈላጊ የሥራ ቁሣቁሶች፣ ፈጣን የመረጃ መረብና አለማቀፋዊ እውቀት እንዲሁም ሁለገብ የቢዝነስ ልማት አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

WHEREAS, it has been found appropriate to enable the entrepreneurs get, by synergizing their time and money, the required working materials, quick information network and global knowledge as well as the overall business development service taking in to account the current shortage of professional in the Information and Communication Technology sector and hence to widen the opportunities of the community benefitting there from;

ዜጎች በተናጠልም ሆነ በጋራ ተደራጅተው መቀጠርን ብቻ ከሚጠብቁ ይልቅ የየራሣቸውን ተቋማት መመስረት ይቻላቸው ዘንድ በገበያ ጥናት፣ በንግድ አመራር ክህሎት ግንባታና በመረጃ አሰባሰብ ተግባራት የሚታገዙበትን አደረጃጀትና አሠራር መፍጠር በማስፈለጉ፣

WHEREAS, it has been necessary to create a structure and a working procedure in which citizens may be assisted in the marketing study, business management skills development and information gathering activities, having been organized individually or in common, with a view to enabling them establish their own firms rather than solely looking for recruitment;

ለዚሁ ያመች ዘንድ ቀደም ሲል የክልሉ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ልማት ኤጀንሲ የተቋቋመበትን ደንብ ቁጥር 72/2002 ዓ.ም. አንዳንድ ድንጋጌዎች መርምሮ ማሻሻልና ተጨማሪ አንቀጾችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

WHEREAS, it has, to that end, been found necessary to review and amend some of the earlier provisions of the Regional Information and communication Technology Development Agency Establishment Regulation No. 72/2009 and thereby incorporate additional articles therein;

www.abyssinialaw.com



የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለዉ የክልሉ ህገመንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 176/2003 ዓ.ም አንቀጽ 35 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, pursuant to the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub-Art. /7/ of the Revised Regional Constitution and Art. 35 of the Executive Organs' Re-establishment and Determination of their Powers and Duties Proclamation No 176/2010, hereby issues this regulation.

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ልማት አጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 100/2004 ዓ.ም' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "the Information and Communication Technology Development Agency Establishment Regulation Amendment, Council of Regional Government Regulation No. 100/2012".

## 2. ማሻሻያ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 72/2002 ዓ.ም. እንደሚከተለው በዚህ ደንብ ተሻሽሏል፡

ሀ. የደንቡ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ /4/ ተሰርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 ተተክቷል፡-

4. "ካምፓኒ" ማለት ኤጀንሲው በዚህ ደንብ መሠረት ወደሚያደራጀው ማዕከል የሚገቡ የአይሲቲ ሥራ ፈጣሪዎች የሚያቋቁሙት የንግድ ድርጅት ነው፡፡

ለ. የደንቡ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሠርዞ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፡-

2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሐ. ከደንቡ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከቱት 2 አዳዲስ ንዑሳን አንቀጾች በተጨማሪነት ገብተዋል፣

## 2. Amendments

The Amhara National Regional State Information and Communication Technology Development Agency Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 72/2009 is amended by this regulation as follows:

A. Art. 2 Sub Art. 4 of the regulation is deleted and replaced by the new Sub Art. 4 here below:-

4. **"Company"** shall mean a business firm to be organized by the ICT entrepreneurs who would join the center established by the Agency, pursuant to this regulation.

B. Art. 3 Sub Art. 2 of the regulation is deleted and replaced by the new Sub Art. 2 here below:-

2. The accountability of the Agency shall be to the Office of the Head of Government of the National Regional State.

C. The following two new Sub Articles are added next to Sub Art. 3 of Article 4 of the regulation:-

www.abyssinialaw.com



4. በክልሉ ውስጥ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ይበልጥ እንዲስፋፋ፣ እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ዘርፉ በግልና በመንግስት የሚኖረውን የገበያ ትስስር ማጠናከር፣
5. የፈጠራ ሥራዎችን በማበረታታትና በዘርፉ ተጨማሪ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግ የክልሉን ሕዝብ ዘላቂ ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

መ. ከደንቡ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከቱት 4 አዳዲስ ንዑሳን አንቀጾች በተጨማሪነት የገቡ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መግባት ምክንያት ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ወደፊት ተሸጋሽገዋል፡-

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገውን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻለው ዘንድ የራሱን ዘመናዊ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ቢዝነስ ኢንኩቤሽን ማዕከል ያደራጃል፣ የማዕከሉን ድጋፍ ለሚጠይቁ አገልግሎት ፈላጊዎች ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በሚገኙ ባለሙያዎች አማካኝነት ከኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ጋር የተያያዘ የኢንተርፕርነር ሽፕ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ የመስሪያ ቦታና ቁሳቁስ ያቀርባል፤
5. የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ባለሙያዎች ራሣቸውን በካምፓኒነት አደራጅተው በቢዝነስ ለመሠማራት የሚያስችላቸውን እገዛ ይሰጣል፣ በመስፈርቱ መሠረት ካምፓኒዎችን ያስመርቃል፤
6. ለተጠቃሚዎች ከሚያቀርባቸውና ከሚሰጣቸው ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ገቢዎችን ይሰበስባል፣ ገቢውንም ለኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን

4. To strengthen the sector's marketing ties between the private and public sectors by disseminating, developing and utilizing the Information and Communication Technology in the Region.
5. To promote the sustainable benefit of the Regional people by encouraging innovations and causing the creation of additional job opportunities in the sector.

D. The following four new Sub Articles are added next to Sub Art. 3 of Article 6 of the regulation and, due to the insertion of these provisions, the subsequent provisions are shifted to the forefront accordingly:-

4. Establish its own modern Information and Communication Technology Business Incubation Center in order to implement the provision stipulated under Sub Art. 3 of this Article; provide entrepreneurship trainings in relation to the Information and Communication Technology through both the national and international professionals to those service seekers requesting for the support of the service; as well as render the workspace and materials.
5. Render support for the Information and Communication Technology professionals enabling them engage in business having organized themselves as a company; Cause the graduation of companies as per the criteria thereof;
6. Collect revenues from the various services it delivers to customers and deploy the revenue for the activities having to do with the expansion of

www.abyssinialaw.com



ቴክኖሎጅ ማስፋፋት ስራዎች ያውላል፣

7. ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ጋር በመመካከር የማእከሉን የሰው ኃይል አስተዳደርና ጥቅማጥቅም አወሳሰን ስርዓት ይመሰርታል፤ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ በማስወሰን በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ሠ. የደንቡ አንቀጽ 8 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 8 ተተክቷል፡-

**8. ሥለ ዳይሬክተሩ አሿሿምና ተጠሪነት**

1. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ይሆናል፡

2. የዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፡፡

ረ. የደንቡ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር ረ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

ረ. ወቅታዊ የስራ ክንውንና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርቶችን ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ያቀርባል፤

ሰ. የደንቡ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

1. የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተር በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ይሆናል፡፡

ሸ. ከደንቡ አንቀጽ 10 ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከተው አዲስ አንቀጽ 11 በተጨማሪነት የገባ ሲሆን በዚሁ አዲስ አንቀጽ መግባት ምክንያት ተከታዮቹ አንቀጾች ወደፊት ተሸጋሽገዋል፡-

the Information and Communication Technology.

7. In consultation with the Regional Civil Service Bureau, establish the center's man power administration and benefit package and cause the implementation of same upon its submittal to and approval by the Council of the Regional Government.

E. Article 8 of the regulation is deleted and replaced by the new Article 8 as follows:

**8. Appointment and Accountability of the Director General**

1. The Director General of the Agency shall be appointed by the Head of the Regional Government.
2. The Director General shall be accountable to the Head of Government.

F. Art. 9 Sub Art. 2/F/ of the regulation is amended as follows:-

F. Submit the periodic work performance and financial utilization reports to the Office of the Head of Government.

G. Art. 10 Sub Art. 1 of the regulation is amended as follows:-

1. The Deputy Director General of the Agency shall be appointed by the Head of the Regional Government up on his presentation by the Director General.

H. The new Article 11 herebelow is added next to Article 10 of the regulation and, due to the insertion of this new Article, the subsequent Articles are shifted to the forefront accordingly:-

www.abyssinialaw.com



**11. የካምፓኒዎች አመራረጥ፣**

1. ማዕከሉ ካምፓኒዎች የሚመረጡበትን መስፈርት አውጥቶ በኤጀንሲው ያስፀድቃል፡፡
2. ማዕከሉ በማወዳደሪያ መስፈርቶቹ መሠረት ወደ ማዕከሉ የሚገቡትን ካምፓኒዎች ይመርጣል፡፡
3. ምርጫው ግልጽነትና ተጠያቂነትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡
4. ውድድሩ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ዕጩ ተጠቃሚዎች ሁሉ የሚጋብዝ ይሆናል፡፡
5. የተመረጡ ካምፓኒዎች የማዕከሉን ሕግና ደንብ አክብረው እንዲሰሩና ማዕከሉ በሚያቀርባቸው አገልግሎቶች እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡
6. የካምፓኒዎች ቆይታ 2 ዓመት ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ከዚህ ሊያንስ ወይም ሊራዘም ይችላል፡፡

ቀ. የደንቡ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ /1/ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

1. የክልሉ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**3. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ነሐሴ 1 ቀን 2004 ዓ.ም
አያሌው ጐበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

**11. Selection of Companies**

1. The center shall set the selection criteria of the companies and get same approved by the Agency.
2. The center shall select the companies which shall join it in accordance with the selection criteria.
3. The selection shall be conducted in consideration of transparency and accountability.
4. The competition shall have to invite all the relevant candidates found in the Region.
5. The companies selected thereto shall operate respecting the rules and regulations of the center and be entitled to use the services delivered by it.
6. The duration of the companies shall be for two years; provided, however, that it may be elongated or shortened, as deemed necessary.

I. Art. 14 Sub Art. 1 of the regulation is amended as follows:-

1. The Regional Information and Communication Technology Development Agency may issue specific directives necessary for the full implementation of this regulation.

**3. Effective Date**

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 7th day of August,2012
Ayalew Gobezie
Head of Government
of the Amharic National Regional State